## የፆታ ትምህርት አስፈላጊነት፣ የቪዲዮ ቤት ፊልሞችና ወሲብ ነክ ጽሑፎች በወጣቱ ላይ ያላቸው ተፅዕኖ

ሲሳይ ሙጨ

### 1. የጥናቱ ዓላማና አስፈላጊነት

በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ውስጥ የማህበራዊ ኑሮና የባህል ለውጦች እየተከሰቱ ናቸው:: የእነዚህን ለውጦች አያያዝ፣ አመጣጥና ሊያሳድሩ የሚችሉትን ተፅእና የማህበራዊ ሳይንስና የሥነ-ልቡና ጠበብቶች፣ የፖለቲካና የሐይማኖት መሪዎች ሊያጤኑአቸውና ሊጨነቁባቸው ይገባል የሚል ከፍተኛ እምነት በመኖሩ፤

- በትምህርት ቤቶች የሚሰጠውን የፆታ ትምህርትን ብቃትና አስፈላጊነትን ገምግሞ ጥረትን ለመጨመር እንዲቻል፣ የትምህርት ባለሙያዎችንና የተመራማሪዎችን ትኩረት ለመሳብ፣
- የወሲብና የፍቅር መጽሔቶችና በግልፅና በድብቅ ወደ ሀገራችን የሚገቡ የቪዲዮ ቤት ፊልሞች በታዳጊው ወጣት በተለይም በተማሪው ላይ የሚያሣድሩት ተፅዕኖ /ለውጥ/ መጠንና ትክክለኛ አቅጣጫውም መለየት ይኖርበታል የሚል እምነት በመኖሩ ነው::

### 2. የመረጃ አሰባሰብ

ጥናቱ የተመሠረተው በመጠይቅ ላይ ነው:: መጠይቁ ሁለት ዓይነት ሲሆን አንደኛው ለመምህራን፣ ሁለተኛው ደግሞ ለተማሪዎች ነው:: ለመምህራን የተበተነው 23 ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን፣ የአብዛኛው ጥያቄዎች መልስ በምርጫ መልክ የቀረበና ለተወሰኑ ጥያቄዎች መልስ ደግሞ ክፍት ቦታ የተወ ነበር:: ለተማሪዎች የተዘጋጀው 52 ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን፣ የአብዛኛዎቹ ጥያቄዎች መልስ በምርጫ መልክ የቀረበ ነበር:: ለጥቂት ጥያቄዎች ደግሞ ክፍት ቦታ የተወ ነበር:: ጥያቄዎቹ የፆታ ትምህርትን፣ የወሲብ መጽሔቶችንና የቪዲዮ ቤት ፊልሞችን የሚመለከቱ ነበሩ::

የቅዱስት ማርያም ትምህርት ቤት ደግሞ ክርስቲያን ሴቶችን ብቻ የሚያስተምር ነው:: ይህ አይነቱ አመራረጥ ጥሩ አጋጣሚ እንደሚፈጥር ይገመታል::

## የጥናቱ ግኝት

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገራችን ብዙ ሰዎች ስለፆታ ትምህርት ሲወያዩ ይሰማሉ:: ሃሳቡም በብዙ ሰዎች ዘንድ ሲደገፍ በአንዳንድ ሰዎች ተቀባይነት የለውም::

ፆታ የተፈጥሮ ፀጋ በመሆኑ ሰው ከተፈጠረ ጀምሮ አብሮ ያለና እንደ ማንኛውም የሰውነት ክፍል ሕዋሳት በሚያድጉበት ጊዜ አብሮ የሚያድግና የሚጎለምስ ነው:: የፆታ ትምህርት ወጣት ወንዶችና ልጃገረዶች ስለባህሪያቸው ተፈጥሮ በተለይም በአድገታቸው ወቅት ስለሚከሰቱ የአካልና የአስተሳሰብ ለውጦች የሚያውቁበት የትምህርት ዓይነት ነው:: በፆታ ትምህርት በኩል ያለው ትልቁ ችግር ወሲብ ራሱ የስሜት ጉዳይ በመሆኑና ከብዙ የስሜት ሕዋሳት ጋርም የተወሳሰበ በመሆኑ በቀላል መንገድ ለማስረዳት ያስቸግራል:: ወሲባዊነት በማንኛውም የሕይወት ጉዳዮችና ተግባር ላይ ሁለት ተቃራኒ ፆታዎች መኖራቸውን የሚያስገነዝበን ሐቅ ነው:: የወሲብ ባህርይም በአንዱ ወይም በሌላ መልኩ ለሰው ዘር ቀጣይነት በጥንቃቄ አመራር የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው:: የሰው ልጅ የፆታ ባህርይ በአጅጉ በልምድ፣ በትምህርትና በመሳሰሉት የሚሻሻል ሲሆን፣ የወሲብ ሕይወትም የሥነ ልቡና መሠረትነት እንዳለው ሳይኮሎጂስቶች ይናገራሉ::

የወሲብ ባህርይና ተግባር በብዙው በትምህርት ላይ የተመረኮዘ ነው:: በዚህም መሠረት ትምህርት፣ ስሜት፣ እስቦት፣ የወሲብ ቅድመ ገጠመኝ /ልምድ/፣ ምኞት፣ ወዘተ ቀጥተኛ ተፅዕኖ አላቸው:: በመሆኑም በወሲብ ባህርይ ላይ በፆታ ትምህርት አማካኝነት ለውጥ ማምጣት ይቻላል:: ትምህርቱ ጠቃሚና ምክንያታዊ የሆነ የፆታ አመለካከትን ከተከተለ፣ ጤናማ ሲሆን፣ በአንፃሩ ደግሞ ጤናማ ካልሆነ ውጤቱም የዚህ ተቃራኒ ይሆናል:: በጥናቱ ከታቀፉት መምህራን የተገኘው መልስ እንደሚያመለክተው 67.9% ያሁሉ ወጣቶች /ተማሪዎች/ ምንም ዓይነት የፆታ እውቀት እንደሌላቸው ገልጸዋል::

የወጣቶች የፆታ እውቀት ምንጭ ምን እንደሆነ ሲመለሱ፣ 23% ከትምህርት ቤት፣ 10.5% ከቤተሰብ፣ 10.5% ከሐይማኖት ትምህርት፣ 55.2% ከነዚህ ውጭ እንደሆነ ገልፀዋል:: ይህም የሚያመለክተው ቤተሰብና ትምህርት ቤት ዋናዎቹ የፆታ ትምህርት ምንጭ መሆን ሲገባቸው ግዳጃቸውን እንዳልተወጡ ያመለክታል:: በፆታ እውቀት ምንጭነት በሐገራችን ጓደኛ ከቤተሰብና ከትምህርት ቤት የበለጠ ሚና እንዳለው ለማወቅ ይቻላል::

በሀገራችን ወጣቶች የፆታ እውቀት ማግኘት የሚጀምሩት አንደኛ ደረጃ ትምህርትን ከአጠናቀቁ ወደ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲገቡ ነው:: ይህም ስለ ፆታ የተፃፉ ነገሮችን አንብቦ መረዳት በሚጀምርበት ጊዜ መሆኑ ነው:: ይህ ደግሞ በልጁ አስተዳደግ ላይ የቤተሰብን ሚና በጣም ዝቅ ያደርገዋል:: ምክንያቱም ሕፃን ስለአካሉ እድገትና ስለ ዝንባሌው መጀመሪያ ሃሳብ ማግኘት የሚጀምረው ከቤተሰቡ በመሆኑ ነው:: የአካሉን ተግባራት፣ ስለሚከለከሉትና ስለማይከለከሉ ነገሮች ድምፅ በሌለው ግንኙነት ማወቅ የሚጀምረው አካሉ ለዚህ ብቁ ከመሆኑ በፊት ነው::

ወላጆች በተገቢው እድሜ ከልጆቻቸው ጋር መለዋወጥ የሚገባቸውን ሀሳብ ሳይለዋወጡ ከቀሩ፣ ለልጆች መስጠት ከሚገባቸው አስፈላጊ ነገሮች ዋናውን እንዳጎደሉ ይቆጠራል:: ምክንያቱም ሕፃናት በቀደመ ጉርምስናቸው ነው ከወላጆች ጋር ስለፆታ በሚገባ የሚጠይቁትና የሚነጋገሩት:: ከጉርምስና ጊዜ በኋላ በወላጆቻቸው ላይ ስለሚያምጹ ነገሮች ሁሉ ይወሳሰባሉ:: የዕድሜ ልዩነት ነፃ የመሆን ፍላጎት፣ በራስ መተማመን የጓደኛ ተጽዕኖ በዚህ የጉርምስና ጊዜ ቤተሰብ የፆታን ጉዳይ በሚመለከት መጠየቅና መማከር ከሚገባቸው ሁሉ የመጨረሻው ይሆናል::

## የፆታ ትምህርት ዓላማዎች

የፆታ ትምህርት የሚከተሉት ዓላማዎች ሊኖሩት ይገባል::

1. በተገቢው የእድሜ ደረጃ የሕፃናት የማወቅና የመጠየቅ ፍላጎት ጤናማ መሆኑን ለማረጋገጥ እና ለማደፋፈር
2. በአዲስ ሕይወት አፈጣጠር ላይ የሚኖራቸውን አድናቆት ለማደፋፈርና ተዋልዶዊ ዝንባሌአቸውንም ጤናማ እድገትን እንዲይዝ ለማድረግ፣

3. ስለማዋለጃ አካላት ገንዘብ ለመስጠትና ሕፃናትም በጕርምስና ጊዜአቸው ስለሚከሰቱ አካላዊ ለውጦች ዝግጁ ለማድረግ ሂደቱም ጤናማ መሆኑን ለማስረዳትና ለማረጋገጥ::

82.9% ከተማሪዎች፣ 74.25% ከመምህራን፣ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ የፆታ ትምህርት በሀገራችን ቱጢባጥ ሁኔታ የተገናዘበና በጥራቱም ሆነ በይዘቱ በቀ ዜጋን ማፍራት የሚችል ትምህርት እስካሁን አልተሰጠም:: ቱጢባጥና ውጤታማ የሆነ የፆታ ትምህርት ለመስጠት ችግሮቹ የሚከተሉት ናቸው::

- በሙያው የሰለጠነ የሰው ኃይልና የመማሪያ መጽሐፍት አለመኖር፣
- በትምህርት ሚኒስቴር በኩል በሥርዓተ-ትምህርት ዕቅድ ውስጥ ባለመታቀፉ፣
- ይህንን ትምህርት ለወጣቶች የመስጠቱ ብቃትና ፍላጐት ባለመኖሩ፣ ትምህርቱ በማንኛውም ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሳይሰጥ ቆይቷል:: አሁንም እስከ መቼ በዚህ ሁኔታ እንደሚቀይ አይታወቅም::

የፆታ ትምህርት ለታዳጊዎች፣ ለወጣቶች፣ እንዲሁም ለጐልማሶች ቢሰጥ ጥቃሚ ሲሆን፣ በይበልጥ ለወጣቱ በተጠናከረ መልኩ መሰጠት ይኖርበታል:: ምክንያቱም ከሕብረተሰቡ ውስጥ አብዛኛው አጅ ወጣት ከመሆኑም በላይ ለስህተት የማጋለጠውም ይህ ክፍል በመሆኑ ነው::

- በከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሚማሩ ወጣቶች መካከል 50% የሚሆኑት የተቃራኒ ፆታ ጓደኛ አላቸው:: ይህም ጓደኝነት ዓላማው ለመዝናናትና በትምህርት ለመረዳዳት ሲሆን፣ ዘላቂ ትዳር ዓላማ ያላቸው ከ5% በታች ናቸው::
- 67.4% ወጣቶች ስለአባለዘር በስታዎችና ስለወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎች እውቀት የሌላቸው ናቸው::
- በአገራችን ራሱን የቻለ የፆታ ትምህርት ከቤት ጀምሮ እስከ ትምህርት ቤት ድረስ ጠቀለለ ባለመልኩ አይሰጥም ብሎ መደምደም ይቻላል:: ይሁን እንጂ አንዳንድ የተማሩ ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ስለፆታቸው ለማስተማር ፍላጐቱና ሙከራው ያለ ይመስላል:: እንዲሁም በትምህርት ቤቶች በሳይንስ ትምህርት ውስጥ አልፎ አልፎ ፆታ ነክ ጉዳዮች ይጠቃቀሳሉ:: ይሁን እንጂ አመርቂ አይደሉም::

## ወሲብ ነክ መጽሔቶች በወጣቶች ላይ የሚኖራቸው ተጽዕኖ

ምንም ዓይነት በፆታና በወሲብ ላይ የተፃፈ መረጃ በሌለባት አገራችን መጽሔቶች ይዘውት የሚጡት ነገር ለውይይት መነሻ፣ እንዲሁም በምሁራን የሚሰጡት ትንታኔዎች ለልምድና ለጥንቃቄ እንደሚረዳ የሚያምኑ ወጣቶችና መምህራን ቁጥር ጥቂት ነው:: 45.5% ያህሉ ተሳታፊዎች መጽሔቶቹ ለወጣቶች አላስፈላጊና ጎጂ እንደሆኑ ያምናሉ:: ምክንያቶችም የወጣቶችን ዝንባሌ በወሲብ ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ በማድረግና ለአልባሌ ልምዱ በማጋለጥ ለትምህርት ያላቸውን ንቃት ይቀንሳል:: ባጭሩ "ነውር" በማስፋፋት የወጣቶችን መልካም ሥነ-ምግባር ያበላሻል ተብሎ ይታመናል::

- ወጣት ተማሪዎች ስለወሲብ-ነክ ጉዳዮች የተፃፉ ነገሮችን የማግኘት ፍላጎታቸው በጣም ከፍተኛ ነው:: 97.9% እነዚህን የወሲብ መጽሔቶች አንብበዋል:: የመጽሔቶቹ ምንጭም በአብዛኛው ቤተሰብ የገዛቸውን ከማንበብ እንደሆነ ታውቋል::

ጽሑፎችን አንብበው ሲጨርሱ ሁሉም ወጣቶች /100%/ ያነበቡትን የመሞከር ፍላጎት ያድርባቸዋል::

- 62% መምህራን መጽሔቶቹ ለወጣቶች ጎጂ ተፅዕኖ እንዳላቸው አረጋግጠዋል:: በመምህራን አስተያየት የመጽሔቶቹ ይዘት ለአንዳንድ ትምህርትና ለጥንቃቄ የሚረዳ ቢሆንም ለወጣቶች ግን ጎጂ መሆኑን ይስማሙበታል::

- ከቀየው ባህላችንና ልማዳችን የተገኘውን ጥቅም መመዘን ባንችልም፣ አሁን በፍጥነት ነባሩን ባህል በመሸርሸር ላይ የሚገኙና መጽሔቶች ይዘውት የሚወጡት መጣጥፍ በ/52.8% የቀየውን ባህላችንና ልማዳችን በእጅጉ እንደሚቃረን ታውቋል:: በተለይ በስዕልና በፎቶግራፍ መደገፋቸውን ባህል አፍራሽነታቸውን ይበልጥ ያጎላዋል፤ አቀራረቡና የቃላት አመራረጡም ያልተለመደ በመሆኑ በአደሚ ለገፋት አስደንጋጭና አሸማቃቂ እንደሆነ ታውቋል::

የቪዲዮ ቤት ፊልም ከሚከታተሉ ወጣቶች መካከል 62% በፊልሙ ተገፋፍተው ያልታሰበና ያልተጠበቀ ስህተት እንደማይፈፅሙና 38% ግን በፊልሙ ተገፋፍተው ያልጠበቁትንና ያላሰቡትን ድርጊት እንደሚፈጽሙ ታውቋል:: 69.9% ወላጆች የቪዲዮ ቤት ፊልሞች ለልጆቻቸው አስፈላጊ እንዳልሆኑ በመገንዘብ ተቃውሞ ያሰማሉ:: 73% አጠቃላይ ሕብረተሰቡ ያልተመረጡ የቪዲዮ ቤት ፊልሞች ለወጣቶች ጥሩ እንዳልሆኑ አስተያየት ሲሰጡ ይሰማሉ::

## ማጠቃለያ

ተጨባጭና መፍትሔ ሰጭ የሆነ የፆታ ትምህርት ለወጣቶች በጣም አስፈላጊ በመሆኑ፣ የወቅቱ ወሲብና ፍቅር-ነክ መጽሔቶች የቪዲዮ ቤት ፊልሞች በወጣቶች ሥነ-ምግባር ላይ ለውጥ እያስከተሉ በመሆናቸው፣ ሁኔታው ሙሉ በሙሉ ከቁጥጥር ውጭ ከመሆኑ በፊት ጠቃሚ መፍትሔ ሊሆን የሚችል የተሟላ የፆታ ትምህርት መስጠት እንዳለበት አጥኚው ያምናል::

ወሲብና ፍቅር-ነክ መጽሔቶች ጎጂ ናቸው ብሎ መደምደሙ ጥቅምና ጉዳቱን አለማመዛዘን በመሆኑ፣ እነዚሁ መጣጥፎች ለልምዱ፣ ለጥንቃቄና ለአጠቃላይ እውቀት ለጎልማሶች በአጠቃላይ፣ ለወጣቶች ደግሞ በከፊል ስለሚጠቅሙ በተጠናና በተገናዘበ መልኩ ቢዘጋጁና ወጣቱ እንዲያገኛቸው ቢደረግ ለተደበቁና ለተከለከለ ነገር ወጣቶች ያላቸውን የማግኘት ፍላጐት ከማርካቱም በላይ ጥቅም ሊሰጥ ይችላል::

የቪዲዮ ቤት ፊልሞች ኃላፊነት በሚሰማቸው ግለሰቦች የተመረጡ ለሕፃናትና ለወጣቶች ተስማሚ መሆናቸው የተረጋገጠ ፊልሞችን ቢያሳዩ የእረፍት ጊዜ ማሳለፊያ ለሚያሳዩትም ግለሰቦች የገቢ ምንጭ ሊሆኑ ይችላል:: ቪዲዮ የሚያሳዩ ግለሰቦችም ጥናቱ የተካሄደባቸውን ፊልሞች የሚያገኙበት ማዕከል ቢኖርና ከዚያ ውጭ ለብልግና ለጋጠወጥነት የሚጋብዙትን በሚያሳዩ ላይ የቀበሌ መስተዳድር ጠበቅ ያለ ቁጥጥር ቢያደርግባቸው ጥሩ ይመስለናል::

ት ር ጉ ም ና  ይ ዘ ቱ

## ጠቅላላ ትምህርት

Action ድርጊት
Analysis of variance የልይይት ትንተና
Annual ከረም
Anticline አብጥ
Anticlockwise ኢሳስትያ
Base line study መነሻ ጥናት
Combination ድበላ
Control experiment ሙከረት
Catastrophy መቅሰፍት
Contamination ብክላ
Correlation ዝምድና
Censoring ገደባ
Coefficient ጠቋሚ
Comet ጅራታም ኮከብ
Coupling ቀንጅት
Dispersion ብተና
Dissociation ገመሳ
Deductive reasoning መንሲአዊ ስመክኖ
Demography ሕዝብ– ነክ ጥናት
Depreciate እሴት መቀነስ
Deciduous ቅጠለ–ረገፍ /ርጋፊ/
Experience ገጠመኝ
Experiment ሙከረት
Extraction ምዝመዛ
Emission ፍልቀት
Excite ማጦፍ

Empirical ለምዳዊ

Formulation ቀመራ

Fluorescence ፋና

Germ ተውሳክ

Germ cell ስርጊ ሕዋስ

Herb ዘረበር

Hibernation ሽሽጋ

Hetrogeneous ደበሳ /ሌ ዩዩ/

Hypothetical cohort ፍጥር ተጣኝ

Hypothetical Population ፍጥር አከብ

Irritability ስሜት ቀስ ቀሳ /እንጭርጭርት/

Infinite ኢውሱን

Judgement sample ገለኛ ናሙና

Nutrient ንጥር ምገብ

Mode ዘወትር፡ ስሌት

Operation ክንዋኔ

Oscillation ውዝ ዋዜ

Partial parasite ከፊል ጥገኛ

Principle መሠረተ ሀሳብ

Procedure ደንብ

Process ሂደት

Rate የፍጆታ ጊዜ

Real income ጭብጥ ገቢ

Rejuvenated እንሰርር

Rotation ዑደት

Roughage ብርእ እህል

Reacton ገሳቢ

Suspension ጉሽ /እንጥልጥል/

System ሥርዐት

Sedentary farmers እርግ ገበሬዎች /ኑዋሪ/

Sex composition ጾታ ዝንቅ /ጾታዊ /

Stalagmite ርገርጌ

Standard time ዱንገገ ጊዜ /መደበኛ/

Staple food ቋሚ መብል

Sublimation ስለመት

Sub-saharan ታች ሰሐራ

Subsistence farming ቋያ ግብርና

Survey ቅኝት

Semen ፍስ

Symmetry ምጥጥን

Ultra ሰካለፍ

Volumetric analysis ስፍረታዊ ትንተና

## ልዩ ትምህርት

Disability የአካል ጉዳተኛ

Visual impairment ማየት የተሳነው

- -Totaly Blind ዓይነ ሥውር
- -Weak sighted የማየት ድክመት

Hearing impairment መስማት የተሣነው

- - Completely Deaf ፍፁም መስማት የማይችል
- - Hard-of-hearing የመስማት ችሎታው የደከመ

Mobility (Motor) disorder የሰውነት እንቅስቃሴ መዛባት

Intellectual disability የአእምሮ ዝግመት

- -Mild disability መጠነኛ የአእምሮ ጉዳት
- -Moderate disability መካከለኛ የአእምሮ ዝግመት /ጉዳት/

-Profound disability ከፍተኛ የሆነ የአእምሮ ዝግመት

Behavioral problems የባህሪ መዛባት ችግር

- -Hyperactive ከመጠን በላይ አካላዊ እንቅስቃሴ የሚያደርግ
- -Hypoactive መጠነኛ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ፣ ራሱን ያገለለና ዝምታ የሚያጠቃው

Speech and Language Problem የቋንቋና የአነጋገር ችግሮች

Multiple Disability ድርብርብ የአካል ጉዳት

- -Deaf and blind መስማትና ማየት የተሳነው

Chronic Health Conditions ሥር የሰደደ ውስጣዊ ደዌ

- -Epilepsy የሚጥል በሽታ
- -Leprosy የስጋ ደዌ በሽታ
- -The Educable የቀለም ትምህርት መማር የሚችሉ
- -The Trainable መሰልጠን የሚችሉ.

-Non-Trainable መሰልጠን የሚያዳግታቸው

-The Lingually impaired የቋንቋ ችግር ያለባቸው

-Delayed Language Development (alalia) ዳተኛ የቋንቋ እድገት

-Stuttering ኢር ቶ አንደበት / ተብታ ገነት/

-Agrammatism ኢሰ ዋሰ ዋዊ

-Stammering (dyslalia) መኮላ ተፍ